# አባ ጃሌው!

*“ክፉውን በክፉ አትቃወሙት፣ ግራው ፊትህን ለሚመታህ የቀኙን ስጠው... ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ የሚረግሟችሁን መርቁ...!”*
ማቴ፡ 5፡ 39 ፤ ሉቃ፣ 6፡ 27-28

፩

አባ ጃሌው በሰፈራቸው ከታወቁና አሉ ከሚባሉት ሽማግሌዎች ሲሆኑ በጣም የተከበሩ ሰው ናቸው። የሰፈሩ ሰው ማንኛውም ጉዳይ ሲኖረው ሁሌ የሚጠራው እርሳቸውን ሲሆን፣ ለምሳሌ ለሚስት አማጭ ሰው ሲፈለግ እርሳቸውን ለምኖ ከሽማግሌዎቹ መሃል ካስገባ፣ ተጠያቂው እምቢ ብሎ መመለስ በጣም ይከብደዋል። ለዚህም ሁሌ ይቀናቸዋል፣ ጉዳዩም ቶሎ ይፈጸማል። በመሬት ሆነ በገንዘብ የተጣላውን ለመሸምገል ዘወትር ሰዉ ሁሉ የሚጠራው አባ ጃሌን ነው። ባልና ሚስትም ሲጣሉ ዋና አስታራቂ ከአባ ጃሌው የተሻለ ሌላ የለም? ስለዚህ አባ ጃሌው የኀብረ ሰቡ ዋና ማገርና ምሰሶ ናቸው ቢባል ከሓቁ የራቀ አይሆንም።

አባ ጃሌው ዕድሜያቸው በትክክል ባይታወቅም፣ አሁን እያረጁ ወደ ዘጠና ዓመት እንደ ተጠጉ ይገመታል። ጥልቅ አስተዋይነታቸውና ብልኀነታቸው የታወቀው ገና ድሮ ሲሆን፣ ያኔ የዓርባ ዓመት ዕድሜ ያህል እንኳን የነበራቸው አይመስሉም ነበር። በሰፈሩ ሰርግ ሆኖ አሳላፊ እንዲሆኑ ተመድበው፣ የመጣውን እንግዳ እየተቀበሉ ከዳስ ሲያቀምጡና ሲያስተናግዱ፣ አንዱ ጠጥቶ ሞቅ ያለው በሰፈሩ የታወቀ ልክስክስ፣ በሆነ ነግር ተላከፉቸውና ግርግር ፈጠረ። ሴቶች ወደሚሠሩበት ወጥ ቤትም ካላለፍኩ እያለ፣ ተው አይሆንም ሲሉት፣ ግልፍ ብሎ ዞር አለና በቃሪያ ጥፊ ጆሮአቸውን አጮላቸው። በዳሱም ሰዉ ሁሉም “እ!’ ብሎ ደነገጠ።

አባ ጃሌው ፈጽሞ ያልጠበቁት ነገር ነበር፣ ግን የቁጣ ቃል ሳይናገሩ፣ ፊታቸውን ሳያጠቁሩ፣ ድምፃቸውንም ሰበር ሳያደርጉ፣ ሰውየውን፤ “ና፣ ወንደሜ፣ ግድ የለህም፣ አይዞህ፣ የማጫውትህ አንድ ጉዳይ አለኝ፣ ና እማ!” እያሉ እጁን አጥብቀው ይዘው ውጭ አወጡትና አጋፋሪዎቹን፤ “ስካሩ እስኪበርድለት እንዳይገባ!” ብለው ከዳስ ተመልሰው ገብተው፣ አንዲትም እንዳልሆነ ሰው የአሰላፊነታቸውን ተግባር በሚገባ ቀጠሉ።

አባ ጃሌ ረጋ ያለው ባሕሪያቸው ከዚያ በፊት በሰፈሩ ቢታወቅም እንኳ በይበልጥ አንጸባርቆ ለሰዉ ሁሉ የታየው በዚያን ጊዜ ነው። ሰው ጠጋ እያለ፣ “አባ ጃሌው፣ እንዴት አስቻልዎት? እጅግ የሚደንቁ ትዕግስተኛ ሰው ነዎት!” ሲላቸው፣ “ይህንን ካልቻልኩማ ለአሰላፊነት የማልበቃ ሰው

ነኛ! መቻል አለብኝ እንጂ! እርሱ መች መታኝ፣ የመታኝ ጠላው፣ ወይ ጠጁ እንጂ እርሱ አልመታኝም።” እያሉ ነው አሳስቀው የመለሱላቸው።

## ፪

“አባ ጃሌው” ሊባሉ የቻሉት በሰፈሩ ሰው አጠራር እንጂ ትክክለኛው ስማቸውስ አያሌው ነበር። ከሰፈሩ አሮጊቶች አንዱ፣ ፊደል እንኳን ያልቆጠሩት፣ እማሆይ ወለተ-ጽዮን የሚባሉት አንድ ቀን፤ “አባ አያሌው” ለማለት፤ “አባ ጃሌው!” ብለው ሲጠሯቸው፣ ከዚያን ጊዜ ወዲያ ሁሉም ተቀብሎ፣ ስማቸውን ከአባ አያሌው ወደ አባ ጃሌው ለወጠው። በልጅነት የወጣላቸው ትክክለኛው ስማቸው ተረስቷል። ዛሬ ይኸው በሰፈሩ ሁሉ “አባ ጃሌው” በሚል መጠሪያ ስም ብቻ ነው የሚታወቁት።

አባ ጃሌው ያደጉት በባላገር ገበሬ ሆነው ቢሆንም፣ ልጆቼን ላስተምር ብለው ወደ አውራጃው ከተማ ከተዘዋወሩ ብዙ ዓመታት አልፏቸዋል። የእርሻው መሬታቸውንም ለባለ ሢሶ ገበሬ ሰጥተውት፣ በየዓመቱ በአህያ ጥቂት ዳውላ ገብስ፣ በቆሎና፣ ማሽላም እየተጫነ ይመጣላቸዋል። ከዚህ ለቤታቸው የሚበቃቸውን አስቀርተው፣ ‘ገበያ ደህና ውሏል’ ሲባል ከተማ ወርደው ለቸርቻሪ ነጋዴ ሸጠው ይገላገላሉ። ሌሎች ራሳቸው ከገበያ የሚቸረችሩ ሰዎች፤ “ለነጋዴ ከምትሰጥ ራስህ ብትቸረችረው የተሻለ ገቢ እኮ ታገኛለህ…” ሲሏቸው፣ “ቸርቻሪውስ ምን ይብላ!” ነው የሚሉት። ዋናው ምክንያት ግን ከገበያ ቆመው ከአላፊ አግዳሚው በዋጋ ውጣ-ውረድ የእንካ ስላንትያ ትንንቅ መያያዙን አልፈለጉትም።

አባ ጃሌው በኑሮአቸውም ሁሉ ረጋ ብሎ መመላለስን የሚወዱ ሰው ናቸው። አንድ-አንድ አስቸጋሪ ሰው ሲያጋጥማቸው ገለል ይሉለታል፣ ወይም ከፊታቸው ገለል የሚያደርጉበትን መንገድ ይፈልጋሉ እንጂ፣ መከራከር፣ መጨቃጨቅ፣ እልኸ መያያዝ የሚባል ፍጹም አይወዱም። ሊያገኙት የማይፈልጉትን ሰው ከሩቁ ሲያያዩት መንገዱን አሳብረው ይሄዳሉ እንጂ፣ ካልሆነ ሰው ጋር መላከፍና አፍ መካፈትን አይወዱም።

አባ ጃሌውን አሰተዋዩ አዕምሯቸውና ትዕግሥታቸው በሰፈሩ ሰው ሁሉ ዘንድ ታዋቂነትና ተወዳጅነትን አትርፎላቸዋል። ስለዚህም ለሽምግልና፣ ለአማጭነት ሆነ የተጣሉትን ለማስታረቅ ሁሉም ሰው ይለምናቸዋል። ለሆነ ጉዳይ ምክር ፈላጊውም ሁሉ ከበራቸውና ከደጃፋቸው አይጠፋም። አባ ጃሌው በአውራጃው ከተማ እንዲህ ቢከበሩም እንኳን ተወልደው ባደጉበት በባላገሩ አካበቢ ግን በወጣቶቹ ዘንድ ትዝታቸው መረሳቱ አልቀረም። እርግጥ ስማቸው አልፎ-አልፎ በአዛውንቱና በአሮጊቶቹ

ቢነሳም እንኳን ማንነታቸው ግን ብዙም አይታወቅም። ለዚህም ዋና ምክንያቱ ከተማ ከገቡ ብዙ ዓመታት በማለፉ ነው።

አንድ ቀን በመኸር ወራት ታድያ መሬቱን እንዲያርስ የሰጡት የሚሶው ገበሬ ድንገት በማታ ከተፍ ብሎ ወደ ቤት መጣ። አባ ጃሌም፤ "ምነው ደህናም አይደለህ? አሁን በመኸር ጊዜ፣ ሥራ በበዛበት ወራት ከከተማ ድረስ ምን ጉዳይ ሊያመጣህ ቻለ?" ቢሉት፤ "አረ እኔስ ደህና ነኝ!" ብሎ ያመጣውን ጉዳይ ሳይናገር አደረ። በማግስቱ ግን በማለዳ ተነስቶ፣ እንደ መርዶ ነጋሪ፤ "አስቻለው የተባለ አንድ ጥጋበኛ ጎረምሳ ከአዙሪት ወንዝ ዳር ያለውን መሬት አጥር አጥሮበት ሄዷል..." እያለ፣ እርምዎን ያውጡ በሚል ዓይነት አነጋገር መርዶውን አረዳቸው።

## ፫

አባ ጃሌው ልጆቻቸውን አሳድገው፣ ሁሉም አዲስ አበባ ሄደው በተለያየ መስክ በሥራ ገበታ ላይ ሲገኙ፣ ከሁሉም ታናሹ ልጃቸው ኮሌጅ ልማር ብሎ፣ ወንድሞቹ ይረዱታል። በክረምት ወራት ግን ከአባቱ ቤት እየመጣ ያሳልፋል፣ ስለዚህ "ነገሩስ ነገር ነው፣ ግን ሰይፍ አያማዝዝም!" እንዲሉ፣ መሬታቸውን ማንም ጥጋበኛ አጥር ተክሎ በመቀማቱ ቅር ቢሰኙም እንኳ ብዙም አልተጨነቁም። ከልጆቻቸው ማንኛውም ቢሆን ከአገር ቤት ሄዶ በግብርና የሚሰማራ አይኖርም፣ እርሳቸውም ከከተማው ምቾት ወጥተው ዳግም ወደ ባላገር ኑሮ አይመለሱም። ቢሆንስ ታድያ መሬቱ የአያት፣ የቅድመ-አያት ርስት ነውና ለቅርብ ቤተ ዘመድ ይሰጣል እንጂ ማንም ጥጋበኛ ጐረምሳ እንዴት ይነጥቀዋል! ነገሩ የሚከነክን ነው።

"እስቲ ደግ ነው፣ መክሬ የማደርገውን አደርጋለሁ። እስከዚያው ሂድ ሌሎቹን እርሻዎች እያረስክ ቆይ..." ብለው የሚሶውን ገበሬ በማሰናበት፣ ነገሩን ማሰላሰል ያዙ። እንደ ድሮ ጉልበትና ብርታት ቢኖራቸው ኖሮ ነገሩን ቶሎ ያጣድፉት ነበር፣ ዛሬ ግን እርጅና መጣና፣ ወደ ፍርድ ቤት መመላለሱን ጠልተው፣ ጉዳዩን ለደህና ነገረ-ፈጅ ሰጥተውት ተመለሱ።

ይህ በሆነ ወር እንኳን ሳይሞላው፣ የሆነ ሰው ከባላገር ተልኬ የመጣሁ ነኝ እያለ ዘው ብሎ ከቤት ገባና መልእክቱን ሲነግር፤ "አባታችን፣ አባ ጃሌ፣ ሰላምታ ይድረስዎት። ፍርድ ቤቱን ይተውት፣ እኛ እናስታርቅዎታለን። ለጊዮርጊስ ዕለት ረፋድ ላይ፣ እርሶዎንና አጥር ተከለ የተባለውን፣ ልጅ አስቻለውን ጠርተናችኋልና እንዳይቀሩብን አደራ። በቀጠሮ ቀን ከአዙሪት ወንዝ ዳርቻ ባሉት ግራሮች ስር እንጠብቅዎታለን!" የሚል ቃል ነበር።

አባ ጃሌም፣ "የሚያስታርቅማ ከተገኘ፣ ከፍርድ ቤት ማን ይንከራተታል" ብለው፣ "እሺ፣ ካስታረቃችሁኝስ ደግ፣ እመጣለሁ እንጂ!" የሚል መልስ

ላኩ። በተባለውም ቀን በቅሎ ተዘጋጅታ፣ ከቤት ልጅ አንዱን አስከትለው ተነሱ። በማለዳም እንደ ሰንሰለት ከተያያዙት ተራሮች ጥግ-ጥጉን ይዘው ሲሰግሩ ካረፈዱ በኋላ ከአዙሪት ወንዝ ደረሱ፣ ከተባለው ቦታ አካባቢ መቃረባቸው ነበር። ትንሽ እንደ ተጓዙም በሩቁ ሦስት ግራሮች ከወንዙ ዳር ብቅ ብለው ታዩ። የቀጠሮው ቦታም ከዚያው ነበር።

ወራቱ በልግ ስለ ነበረ አዝርእቱና እሸቱ በመንገዱ ግራና ቀኝ ሜዳውን አልብሶታል። የዱር አበባም ሽታው ከሩቁ ዕውድ-ዕውድ ይላል፣ ንብ፣ ተርብና ልዮ-ልዮ ወፎችም ውር-ውር ይሉ ነበር። አባም ከበቅሎዋቸው ኋላ ያፈናጠጡትን ልጅ፤ “በል ውረድ ልጄ፣ አሁንስ ደርሰናል፣ ምንም አልቀረንም፣ እኒያ ግራሮች ድረስ በእግርህ ተከተለኝ” ብለውት ወርዶ፣ በእግሩ ከኋላ-ኋላቸው መከተል ያዘ።

ከግራሮቹ ጠጋ እንዳሉም ሁለት ሰዎች ሲጠብቋቸው አዩ። ሰዎቹም አባ ጃሌን እንዳዩ፣ ከተቀመጡበት ተነስተው፣ ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ በአክብሮት እጅ ነስተው ተቀበሏቸው። ሰላምታ ከተለዋወጡም በኋላ፤ “አባታችን፣ አባ ጃሌ፣ ይቅርታ ያርጉልን አደከምንዎት፣ ካሉበት ድረስ መምጣት የሚገባንስ እኛው ነበርን፣ ግን ጉዳዩ ያለው ከዚህ ቦታ ስለሆነ፣ እርሰዎን ማድከም የግድ ሆኖብን ነው?” እያሉ ይቅርታ ጠየቁ።

አባ ጃሌም፤ “የለም ልጆቼ፣ ለኔም ነፋስ መቀበያ፣ ከቤት መውጫ ሆነኝ እንጂ፣ ይህ በመሰለ ቀን ትንሽ ሽርሽር፣ ምን ድካም ይባላል?” አሉ።

“እንግዲያው አስቀድመን ጥሪያችንን አክብረው ስለመጡ እናመሰግናለን፣ አሁንም አቶ አስቻለው እንደ መጣ ብዙ አንይዝዎትም፣ በቶሎ ቤትዎ እንዲመለሱ እናደርጋለን፣ ብዙ የሚያስቆይ ነገር አይኖረንም!” አሉ።

አባ ጃሌም፤ “ለመሆኑ ደህና ናችሁ ወይ? አገሩ ሁሉ ሰላም ነው?” አሉ።

ሰዎቹም ሲመልሱ፤ “አባታችን፣ እኛ ደህና ነን፣ አገሩም ሁሉ በእርስዎ ጾምና ጸሎት ሰላም ነው። በልጉም እንደሚያዩት አምሮበታል፣ አሁን በቅርቡ ለዓጨዳና ለዓውድማ ይደርሳል። ዘንድሮ ጥጋብ ነው!” አሉ።

የአገር ሽፍታ የተባሉት ሰዎች ይቅርና የብረት መሣሪያ እና ጠመንጃ፣ አንዲት ጩቤም የሌላቸ፣ ከያዙት ቀጭን ከዘራ ብጤ በእጃቸው አንድም ነገር የሌላቸው ሰዎች ነበሩ። እንዲህ እያወሩና እየተጫወቱ ከአንድ ሰዓት በላይ ካለፈ በኋላ፣ ከሁለቱ መሪ መስሎ የሚታየው፤ “አቶ አስቻለው የሚመጣ አይመስልም፣ በቂ ጊዜ ጠበቅነው ግን አልመጣም። እርስዎን

አባታችንንም በከንቱ አድክመን አጉላላንዎት፣ ይቅርታ! እንግዲያውስ ይሂዱ፣ የቀረውን ለኛ ይተውልን። እኛው እንጨርሰዋለን!” እያለ ተነሳ።

አባ ጃሌም፤ “ተባረኩ ልጆቼ፣ እንደ እናንተ የመሰለ አውራ ከየሰፈሩ እና ከየቦታው በሃገራችን አይጥፋ። ሰውየው ካልመጣ’ማ ምን ይደረግ? በሉ በሰላም ዋሉ።” ብለው በመሰናበት ልጃቸውን አስከትለው ወደ ቤታቸው መንገድ አቀኑ። ከዚያ ትንሽ ራቅ እንዳሉም በቅሎዋን አቁመው ልጁን ከኋላ አፈናጠጡና እየሰገሩ ወደ አውራጃው ከተማ ጉዟቸውን አመሩ።

## ፬

ይህ በሆነ ሳምንት እንኳን ሳይሞላው፣ በአቶ አስቻለው ላይ የደረሰው ጉድ ወሬው በከተማው ይነፍስ ያዘ። ‘ጠርተነው ሳይመጣ የቀረበትን ትዕቢትና ንቀቱ እንዲበርድለት…’ ብለው ሽፍቶቹ በሌሊት ከቤቱ ድረስ ሄደው፣ እጅና እግሩን ጠፍረው በማሰር፣ በሽመል ሙልጭ አድርገው ገርፈው፣ ‘ሁለተኛ አይለምደኝም!’ ብሎ እየጮኸ፣ ተማጥኖና ተገዝቶ፣ ፍዳውን ሁሉ ቆጥሮ፣ አፈር መሬት አብልተው ለቀቁት ይባላል። ብዙ ሳይቆይም ዘመድ ወዳጆቹን አለማምኖ ያቺ አጥር ተነቅላ እንድትነሳ አስደረገ። በሰው እንጂ እርሱ’ማ ምንም ሊያደርግ አይችልም ነበር፣ በግርፋት ቆስሎ የተገጣጠበው ጀርባው እስኪድን ለረዥም ጊዜ የአልጋ ቁራኛ ሆነ አሉ።

በጥጋቡ ያመጣው ጦስ ስለሆነ ከቅርብ ቤተሰቡ በቀር ማንም ያዘነለት አልነበረም። የብዙዉ ሰው አስተያየት፤ ‘በሃገሩ መሬትና ቦታ አልጠፋ! ጥሻውን መንጥሮ፣ የሚለበደውን ለብዶ፣ የራሱ እርሻ ማልማት ይገባው ነበር። በጥጋቡ የሽማግሌው፣ የአባ ጃሌው ንቀት ነው ያጋለጠው! የሰው መሬት ማን ንካ አለው? ደፋር፣ ዓይነ ደረቅ፣ የእጁን አገኘ፣ እሰይ!’ ብቻ የሚል ነበር። አቶ አስቻለው ቀደም ብሎ የቅርብ ቤተ ሰብና ወዳጆቹን ቢያማክር ኖሮ ይህ መች ይመጣበት ነበር? ለሌላው መቀጣጫ ሆኗል።

አባ ጃሌም ስለዚህ ጉዳይ ሲጠየቁ፣ “እኔ ምን አውቃለሁ? እንደ እኔ’ማ ፍርድ ቤት ይወስን ብዬ አመልክቸ ነበር፣ ግን ይህ ጉዳይ በፍርድ ቤት ታይቶ፣ ምስክር ተቆጥሮ፣ ይግባኝ ተብሎ፣ ከላይ በዳኛ ተወስኖ፣ ለፍርድ አሰፈጻሚ ደርሶ በተግባር ላይ እስኪውል ድረስ ብዙ ዓመታት ይፈጃል። ያ ሁሉ እሲኪሆን ታድያ ለጠበቃ፣ ለተላላኪ፣ ለመዝገብ ቤት ፋይል አውጪ፣ ለዳኛ ጉቦ እያሉ ስንት ወጪ አስከትሎ ኪሳራ ላይ ይጥላል። መንግሥት ለሃገሩ ሁሉ የቆመ ስለሆነ ለስንቱ ይዳረሳል? እስኪዳረስ ጊዜ ይፈጃል፣ የተበደለው ሰውም ብዙ ጥቃት ይደርስበታል። እንዲህ የመሰለ አውራ ሲኖር ግን፣ ማንም አለሁ ባይ ባለጌ ጉልበቱን ተማምኖ ወንጀል

ሲፈጽም በቶሎ አርሞ ይቀጣዋል፣ ለተበደለውም ይደርስለታል። ስለዚህ በየአገሩ፣ በየቦታው አውራ አይጥፋ!" ይሉ ነበር።

ይህ ከሆነ በኋላም አባ ጃሌው ብዙ ሳይቆዩ በምስጢር በዚያ በሚሶ ገበሬ እጅ መልእክት ልከው፣ መሬታቸውን ላስመለሱላቸው ሽፍቶች ከልብ ከመነጨ ምስጋና ጋር ማለፊያ የሆነ ሙክት እንዲሰጥ አደረጉ። ይኸም ከፍርድ ቤቱ ክፍያ ጋር ሲመዛዘን ቅንጣትም አይሆንም። ምክንያቱም ለማመልከቻ ጸሐፊና ለፋይሉ ማስመዝገቢያ የወጣው ብቻ እንኳን ቢደመር ከሙክቱ ዋጋ ዕጥፍ ከፍ ብሎ ቢበልጥ እንጂ አያንስም።

## ፭

አባ ጃሌው ዛሬ ብዙውን ጊዜ ጋቢአቸውን ደረብ አድረገው ከአልጋቸው ተጋድመው ነው የሚውሉት። ልጆቻቸው ከአዲስ አበባ ሊጠይቋቸው ሲመጡ፤ "አባባ፣ ምን ይዘንልህ እንምጣ?" ሲሏቸው፣ "ልብስ!" ይላሉ። ልጆቻቸው የሚያመጡላቸውን ልብስ ግን ሲለብሱት ማንም ሰው አይቶት አያውቅም። የሰፈሩ ድሆች ብቅ እያሉ፤ "አባ ጃሌው! እንዴት ሰነበቱ..." እያሉ ሊጠይቋቸው ሲመጡ ልብሶቹን ከአጠገባቸው እያነሱ፤ "እንካ ያውልህ፣ ሽፍነህ፣ ደበቅ አድርገኸው ሂድ!" ብለው መለገስ ነው።

የሰፈሩ ድኻ ሁሉ እየመረቃቸው ለብሶ ይኖራል። እንዲህ እያሉ በሰላም ሲኖሩ ታድያ አንድ ቀን በአውራጃው ከተማ ከታወቁት የማዘጋጃ ቤት ባለ ስልጣኖች አቶ ስንዱ የተባለ ሰርግ ደግሶ፣ ልጁን ዳረ። አባ ጃሌው ታድያ ከቤት ውለው፣ የሰርግ መሂጃ ዘመኑ አልፏቸው፣ ስለ ድግሱ ሰፊ ዝግጅት በወሬ ይሰሙ ነበር። የዛሬን አይበለውና በዚህች የአውራጃ ከተማ አባ ጃሌ ከአማጭነት ጀምሮ አስከ አሰላፊነት ያልተካፈሉበት ሰርግ እንደ ሰርግ የማይቆጠርበት ጊዜ ነበር። የማያልፍ የለም፣ ያም ሁሉ አልፏል።

ሰርጉ በተደገሰበት ማግስት ታድያ አንድ ጉድ ሰተት ብሎ ወደ ቤታቸው አመራ። የተዳረችው የአቶ ስንዱ ልጅ ድንግል ሆና አልቆየችም። ሙሽራው በዚህ ተናድዶና ተቆጥቶ ሙሺሪቱን ከጫጉላ ቤት አባረራት። ቤተ-ሰብ ሁሉ ጉድ እያለ ተሰብስቦ ሲያዝን፣ አባት እና እናት ልጅቱን ለብቻዋ ከመኝታ ቤቷ አስገብተው፣ በጥያቄ እንዲህ ያደረገሽ ማን ነው እያሉ አውጣጧት። "የኔን ድንግል የወሰደው በቀለ ነው።" አለች። አቶ ስንዱም በቀለን እገድላለሁ እያለ መደንፋቱ በከተማው በይፋ ተወራ።

በቀለ የአባ ጃሌው የመጨረሻው ልጃቸው ነው። በእውነትም የኮሌጅ ተማሪ ሆኖ፣ በክረምት-ክረምት ከአዲስ አበባ መጥቶ፣ ከአባቱ ጋር ጊዜ ሲያሳልፍ፣ ከአንዴም ሁለቴ ልጅቱን ይዟት ከቤት መምጣቱ አባ ጃሌው ትዝ አላቸው። ያ ነገር ታድያ ዛሬ ሦስት፣ ወይም አራት ዓመት ገደማ

ሆኖታል። አሁን በቀለ ኮሌጅ ጨርሶ ከጅማ በቡና ቦርድ ሥራ ይዟል። ታድያ ምን ለማድረግ ይቻላል? አባ ጃሌም በልባቸው፣ "ጐሽ የኔ ልጅ!" ቢሉም፣ ምን እንደሚያደርጉ ማሰብና ማሰላሰል ያዙ። አቶ ስንዱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ እርሳቸው አቅጣጫ እንደሚገሰግስ ምንም አልሳቱትም።

አባ ጃሌው፤ 'የልጄን ክብር ገሥሏል… በቀለን እገድለዋለሁ' እያለና እየደነፋ የሚመጣውን አቶ ስንዱን እንዴትና በምን ዓይነትስ ሁኔታ እንደሚቀበሉት ጨነቃቸው። ምን ብለው እንደሚመልሱለትና ምንስ እንደሚሉት ማውጣትና ማውረድ ያዙ። ምን ቢሉት ይሻል ይሆን?

## ፯

አባ ጃሌው አውርደውና አሰላስለው መላ-ምት መቱ፣ አንድ ብልሓትም ፈጠሩ። ከቤት ልጆች አንዱን ጠርተው፤ "ልጄ እስኪ ወረቀትና ብዕር ይዘህልኝ ና። አንድ የምትጽፍልኝ ደብዳቤ፣ የለም፣ ሁለት ደብዳቤዎች ናቸው። ቶሎ በል!" ብለው ጠሩት። ሁለቱን ደብዳቤ እንደ ጻፈላቸውም በቶሎ አንዱን ደብዳቤ ወደ ልጃቸው፣ በፖስታ ቤት ወደ ጅማ ላኩለት። ደብዳቤው ይዘቱ፤ "ልጄ፣ በቀለ! ለአንድ አስቸኳይ ጉዳይ ስለምፈልግህ ሳትውል፣ ሳታድር፣ ዛሬውኑ ስልክ ደውልልኝ…" የሚል ነበር።

ሁለተኛውን ደብዳቤ ግን በትራሳቸው ከተደረደሩት የድሮ ደብዳቤዎች አንዱን ፓስታ ከፍተው በውስጡ ከተቱና ጋቢአቸውን ደራርበው ገደም አሉ። ገደም እንዳሉ ብዙም አልቆየ፣ "የፈሩት ይደርሳል… " እንዲባል፣ አቶ ስንዱ ወድያው ከቤታቸው እየደነፋና እየጮኸ ከተፍ አለ።

አቶ ስንዱ ጤና ይስጥልኝ ብሎ ገብቶ፤ "ተቀመጥ!" ሲሉት፣ ሳይቀመጥ፣ በቁጣ ብው አለና፣ "አባ ጃሌው፣ ዛሬ የመጣሁበት ጉዳይ ልጅዎ በቀለ ልጄን አስካለችን ደፍሮብኝ፣ አዋርዶኛል። የመጣሁበት ምክንያት ካሳ ለመጠየቅ እንዳይመስልዎት። እኔ ሌላ ካሳ አልፈልግም፣ በቀለን በእጄ ልገድለው ነው የመጣሁት። የት ነው ያለው? ይንገሩኝ!" አላቸው።

አባ ጃሌም፤ "ይካሱኝ ብትልስ ምኔን ነው የምክስህ? በል ሂድ ግደለዋ! እኔ ምን ላድርግ? የዛሬ ልጆች ወላጅ የሚመክራቸውን መች ይሰሙና! አንተስ ወልደህ አይተኸው የለ? ምን አድርግ ነው የምትለኝ?" አሉት።

"በቀለ ያለበትን ብቻ ይንገሩኝ፣ የማደርገውንስ እኔ አውቃለሁ!" አለ።

አባ ጃሌም ደብዳቤውን ከጻፈው ልጅ ሌላውን የቤት ለጅ ጠርተው፣ ከትራስጌ ቀደም ብለው ያስቀመጡትን ደብዳቤ አወጡና፤ "ባለፈው ሰሞን በፖስታ የመጣልኝ ነው፣ እስኪ ልጄ አንብብልኝ…" እያሉ ሰጡት።

ልጁም፤ "አባባ፣ ለጤናዎ እንደምን አሉ..." ወዘተ፣ ብሎ ሰላምታውን ካቀረበ በኋላ፣ ስለ ራሱ ጤንነት፣ ቀጥሎም የሥራ ዕድገት አግኝቶ ወደ ሓረር መዘዋወሩን የሚገልጽ ዝርዝርና በቅርቡም ወደ አውራጃው ከተማ መጥቶ እንደሚሰናበታቸው የሚገልጽ ወሬ አበሰረ። ይኸ ሁሉ አባ ጃሌ አስቀድመው ያውጠነጠኑትና የጠመጠሙት ሲሆን፣ በቀለ አባቱን ሊያይ ይመጣል ብሎ አቶ ስንዱ ከዚሁ ተቀምጦ እንዲጠብቅና፣ እሱን ለማደን ወደ ጅማ እንዳይሄድ ያዘጋጁት የተንኮል ደብዳቤ ነበር።

አቶ ስንዱ ይኸንን ሲሰማ፤ "መቼ ነው ደብዳቤው የተጻፈ ብሎ ጠየቀ። አባ ጃሌም አስቀድመው ባውጠነጠኑት የደብዳቤው ዕለት የዛሬ ሦስት ሳምንት አድርገውታል። አቶ ስንዱ፤ "ነገውኑ ወደ ሓረር እገሰግሳለሁ!" እያለ ደጋግሞ ደነፋ። ቀጥሎም፤ "ካልገደልኹት ይኸን ሱሪየን ግልብጬ ነው የምለብሰው። ልጄን ደፍሯት እንዲሁ በከንቱ አይቀርም!" አለ።

አባ ጃሌም፤ "እኔ ምንም የምልህ የለኝም። እንዳልከው ሂድና ግደለው። እውነትህን ነው፤ እኔም ሴት ልጄን ማንም ሰው ቢደፍርብኝ ያው ነው። አልምርም። ሂድ ግደለው!" አሉት።

አቶ ስንዱ ይህ ፈጽሞ ያልጠበቀው መልስ ሆኖበት ግራ ገባውና ምን እንደሚላቸው ጠፋው። አንደበቱ ሁሉ ተሳሰረ። ነገሩን ሲጀምር 'ልጄን እንዳትነካ!' የሚሉት መስሎት ነበር፣ 'ሂድና ግደለው...' የሚል መልስ ሲሰማ ግን የቁጣ መንፈሱ በረድ እያለ መምጣቱ ከፊቱ በግልጽ ይታይ ነበር። ያም ቢሆን እንዳመጣጡ እየፎከረና እየደነፋ ወጣ።

ወጣ እንዳለ ግን አባ ጃሌው የቤት ልጆቻቸውን፤ "እስኪ ልጄን መግደል ቀርቶ የፊቱን ዝንብ እሽ ሲል አያለሁ! ወይ ጉድ! የዛሬ ሴቶች ወንድ ሲያዩ የሚሆኑትን እያጡ፣ ሲያቅበጠበጣቸው፣ እራሷ ለምናውስ ቢሆን ማን ያውቃል? አስገድዶኝ ነው ልትል ይሆን? ታድያ'ማ ከቤቱ ድረስ ምን ያመላለሳት ነበር? ደግ አደረገ! የወንድ ልጅ 'ሰረቀ፣ ዋሸ' ተብሎ አይወራበት እንጂ፣ ይኸ'ማ የጀግና ሥራ ነው የሠራው፣ ጐሽ!" አሉ።

አቶ ስንዱ እንደፎከረው በማግስቱ ማለዳ ገስግሶ፣ በአውቶቡስ ተሳፍሮ ሓረር መሄዱን ሰሙ። አባ ጃሌ የጻፉት ሁለተኛው ደብዳቤም ከጥቂት ቀናት በኋላ ደርሶ፣ ልጃቸው በቀለ ከጅማ በጎረቤት ስልክ ደወለላቸው። አባ ጃሌውም በከተማው የሆነውን ሁሉ ዘርዝረው በማስረዳት፣ "ልጄ! ተጠንቀቅ፣ ለጥቂት ቀናት ነገሩ እስኪበርድ ድረስ ከወንድሞችህ ዘንድ፣ አዲስ አበባ ሂድና ተደብቀህ ቆይ... ነገሩ ሲበርድ እኛው እንነግርሃለን።" ብለው መክረው አስጠነቀቁት።

አቶ ስንዱ ሓረር ለሳምንት ያህል ተንከራትቶ፣ በቀለን ቢያጠያይቅ ሳያገኘው ቀረ። ምናልባት ገና ከጅማ አልተዘዋወረ ይሆናል በማለት ወደ ጅማ ሄደ። ከዚያም አጠያይቆ በቀለን በሥራ የሚያውቁት ሰዎች አገኘ፣ ግን በጅማ ከተማ ለጥቂት ቀናት አለመታየቱን እንጂ ወዴት እንደ ሄደ ለማወቅ አልቻለም። ተስፋ ቆርጦ በሁለተኛው ሳምንት ከቤቱ ተመለሰ። የከተማው የማዘጋጃ ቤት ቋሚ ሠራተኛ በመሆኑ፣ በልጁ ሰርግ ሰሞን በወሰደው ዕረፍት ላይ ተጨምሮ የዓመት ዕረፍቱ ቀናቶች ሊያልቁበት ሆነና፣ ሳይወድ ከሥራው ገበታ እንዲመለስ ተገደደ።

"የዋለ፣ ያደረ ነገር አትጥላ!" እንዲባል፣ ውሎ አድሮ ነገሩ እየቀዘቀዘ መጣ፣ አባ ጃሌውም አቶ ስንዱን እንታረቅ ሲሉ ሽማግሌዎች ላኩበት።

## ፯

ከአቶ ስንዱ ዘንድ የተላኩት ሽማግሎች ከቤቱ ገብተው፤ "አባ ጃሌው ራሳቸው መጥተው፣ በጉልበታቸው ከመሬት ተንበርክከው ይቅርታ ቢጠይቁህ በወደዱ ነበር። ግን እንዳየኻቸው አርጅተው የአልጋ ቁራኛ ሆነዋል። 'ሰው ቂም ይዞብኝ እንዳልሞት' እያሉ በጣም ተጨንቀው ነው የላኩን። ታድያ ቂምህን አውርጃለሁ በላቸው!" አሉት።

እርሱም፤ "እኔ ከእርሳቸው መች ተጣላሁ፣ የምን ቂም ኖሮኝ ነው ዕርቅ የሚያስፈልገን? ያልተጣላ ይታረቃል እንዴ?" እያለ አንገራገረ።

እነርሱም ቀጥለው፤ "እስኪ ከዛሬ ልጆች ማን ነው የአባት፣ የእናት ምክር የሚሰማ? ምን ያድርጉ ብለሃቸው ነው? እሳቸውም እንደሆኑ ከአፋቸው የሰማኸው አይደለም እንዴ? የልጃቸውን ጥፋት ተቀብለው፣ 'ሂድ ግደል!' አሉ እንጂ፣ ልጄ ነው ብለው ጥፋቱን ለመሸፈን አልሞከሩ፣ አላንገራገሩ! በል እንግዲያው አሁን እንዳልካት ከአባ ጃሌው ጋር ቂም ከሌለህ፣ አሁኑ ሄደህ፤ 'አኔ በእርሰዎ ላይ ቂም የለኝምና፣ 'ይቅር!' ብያለሁ' በላቸው እና በሰላም ይሙቱ። ይቅር ለእግዚሄር ነው!" እያሉ ለመኑት፣ ተማጠኑት።

አቶ ስንዱ የተላኩትን ሦስት ሽማግሌዎች፣ የገፋ ዕድሜያቸው፣ የሸበተው ጺማቸው፣ የተመለጡ ራሶቻቸውን፣ ከደረቡት ነጭ ጋቢ ጋር፣ ድንቅና ዕጹብ ግርማ ሞገስ አልብሷቸው ሲያይ፣ ከቤተክርስትያን ያለውን የሦስቱ ሥላሴን ምስል ያየ ሆኖ ተሰማው፣ እንዴት ብሎ እምቢ ይበል? ወዲህ፣ ወድያ አያለ፣ የባጥ የቆጡን እያወጣና እያወረደ ዘላበደ፣ ለጥቂት ጊዜም አቅማማ። እነርሱስ መች ዋዛ፤ "እሺ እስክትለን ከተቀመጥንበት አንነሳም፣ ከቤትህም አንወጣም!" ብለው ወጥረው ያዙት፣ መፈናፈኛም አሳጡት።

ቢጨንቀውና መውጫ ቢያጣ፤ “ካላችሁስ እንግዴህ ምን ላድርግ፣ እሺ!” አላቸው። ሦስቱም ተራ በተራ እየተነሱ፣ አንቀው እየሳሙ፣ “እመቤታችን እግዚትነ ማርያም ራሷ እሺ ትበልህ፣ ተባረክ ልጃችን፣ ረዥም ዕድሜና ሙሉ እንጀራም ጨምሮ፣ አብዝቶ ይስጥህ!” እያሉ መረቁት።

አቶ ስንዱም፤ “አሜን፣ አሜን!” እያለ ምርቃታቸውን ተቀበለ።

“በል እንግዴህ ዛሬ፣ ነገ ሳትል፣ ፈጥነህ ሄደህ ጠይቃቸው፣ የሽማግሌ ነገር አይታወቅም፣ ብዙ ቀን የቀራቸውም አይመስሉም። ንስሓ ገብተው፣ ነፍሳቸውን አዘጋጅተው፣ ስጋ-ወደሙ እንዳይቀበሉ፣ አንተ የያዝክባቸው ቂም በልባቸው ገብቶ፣ እስካሁን የጋረዳቸው እሱ ብቻ ነው!” አሉት።

“እሺ፣ እሺ! አባቶቼ፣ ያላችሁኝን ሁሉ በቶሎ እፈጽማለሁ!” ብሎ ቃል ገባላቸው። ከዚያም ሽማግሌዎቹ ተነስተው ወደ መጡበት ተመለሱ።

የአባ ጃሌው አሰተዋይ ጥበብና ዘዴ እንዲያ ቦግ ብሎ ሊነድድ እና አገር ሊያቀጣጥል ተነስቶ የነበረውን እሳት አበረደው። አቶ ስንዱም በገባው ቃል መሰረት ከጥቂት ቀናት በኋላ ከአባ ጃሌው ቤት ሄዶ ቂሙን ማውረዱ ሊገልጽ ሲገባ፣ እሳቸውም በቀረችው ጉልበታቸው፤

“ልጄ! ልጄ! እሰይ፣ እሰይ! እንኳን’ማ መጣህልኝ!” እያሉ ከአልጋ ሊነሱ ሲሞክሩ፣ ያረጀውና የሳሳው አካላታቸውን አይቶ አንጀቱ ክልውስውስ አለበት። የበፊት ንዴቱ ወዴት እንደ ገባ እርግፍ አድርጎ ረሳው።

“የለም! የለም አባቴ! አይነሱ! አይነሱ! አይገባም፣ አረ ፈጽሞ አይገባም!” እያለ እንዳይነሱ ለመከልከል ወደ እርሳቸው ጠጋ ሲል፣ አባ ጃሌውም፤ “ይቅር በለኝ ልጄ፣ ይቅር በለኝ!” እያሉ ተንገዳግደው ከላዩ ዝልፈልፍ ብለው ተጠመጠሙበት። እንደምንም ደጋግፎ ከአልጋው መልሷቸው፤

“እኔ እርስዎን መች ተቀየምሁ? አረ ይተውኝ አባቴ፣ ደግሞስ ምን ቂምና ይቅር የሚባል ነገር ኖሮ ነው?” ብሎ ሲላቸው፣ ሁለቱም ተቃቅፈው፣ ተላቅሰው፣ ‘ይቅር! ይቅር ለግዚሄር!’ ተባብለው ተሳሳሙ።

ወድያውም ቡናው ተፈልቶ፣ የማሽላ ቆሎ ፍንድሻ ተፈንድቶ፣ አብረው እያወሩና እየተጫወቱ እኽል ውሃ ብለው ታረቁ። ከዚያ ቀን ጀምሮ፤ ‘አሁኑኑ እገድለዋለሁ! በቀለን ካለበት ውለዱ፣ የታለ?’ እያለ ሲፎክር የነበረው አቶ ስንዱም ቂሙና ቁጣውን እርግፍ አድርጎ ረሳው።

በሁለቱም ቤት መካከል ሰላም ወረደ። መታረቃቸውም በሰፈሩ ሁሉ በይፋ ታወቀ። ከዚያማ ወድያ አቶ ስንዱ ዋና ቤተኛና ዘመድ ሆኖ አባ ጃሌውን ዘወትር እየተመላለሰ ይጠይቃቸው ነበር። እንግዴህ አባ ጀሌው

በቀለ ሊጠይቃቸው ሲመጣ አንዲት ጊደር ወይ መሲና ብጤ አስይዘው ከአቶ ስንዱ ቤት ሄዶ ይቅርታ እንዲጠይቅ ይልኩታል። ከዚያም ወድያ የቂሙ ጉዳይ አበቃ፣ ተከተተ ማለት ነው። ለጥፋት ታጥቆ የመሚጣውን ጠላት ተቀብሎ ወዳጅ ማድረግ ረቂቅ ጥበብና ዘዴ የሚጠይቅ ነው።

## መደምደሚያ፦

በተፈጥሮ እጅግ ከሚደንቁ ረቂቅ ነገሮች አንዱ፤ ዘወትር አካላታችንን ለመጉዳትና ለማጥቃት፣ ከሆነላቸውም ለማጥፋት የሚችሉ ብዙ ዓይነት ጠንቀ-ጎዋሳት ወደ ውስጣችን ይገባሉ። ሰውነታችንም ሁሌ ሲዋጋቸው ይኖራል። የሚጎዱትንና የማይጠቅሙትን ጠንቀ-ጎዋሳት በብዙ ዘዴዎች አንጥሮና አበጥሮ እየለየ በብጉር፣ በላብ፣ በሽንትና በእዳሪ መልክ ውጭ አውጥቶ ሲጥል፣ አንዳንዶቹን ግን በልዩ ዘዴ አባብሎ በመያዝ በተለያዩ ብልቶች ውስጥ በማስቀመጥ በብዙ አገልግሎት ላይ ያውላቸዋል።

በጨጓራችንና በሌላውም መላው የሰውነታችን ክፍሎች ከሚኖሩት ብዙ ዓይነት ጠንቀ-ጎዋሳት ጋር፣ በሰውነታችንና በጎዋሳቱ መካከል ግሩምና ረቂቅ የሆነ ስምምነትና መግባባት በመፈጠሩ፣ ካለ እነርሱ ልንኖር ቀርቶ፣ ለደቂቃም ቆመን ልንሄድና ልንተነፍስም አንችልም። ጠንቀ-ጎዋሳቱ ለእኛ የሚጠቅሙ ልዩ-ልዩ ተግባሮችን እየሠሩ ሲያገለግሉን፣ እኛም የምግብ ምንጭ፣ መኖሪያ፣ መጠጊያና ከለላም ሆነናቸው በስምምነት እንኖራለን።



ለመጉዳት የሚመጣውን ጠላት አባብሎና አግባብቶ የልብ ወዳጅ ማድረግ ጥልቅ አስተዋይነትና ዘዴ ሲጠይቅ፣ በዓለም ላይ ከዚያ የበለጠ ጥበብ አለ ብሎ ለማለት ያዳግታል። ይህን ጥበብ የዓለም መሪዎች በሥራ ላይ ቢያውሉት ኖሮ ምድር ገነት በሆነች ነበር።

አባ ጃሌው ፊዴል ያልቆጠሩ መሃይም ናቸው፣ ግን ተፈጥሮ ባደላቸው ብሩህና አስተዋይ አዕምሮ ይህንን ጥልቅ የተፈጥሮ ጥብበ ደርሰውበታል። በሕይወታቸው ዘመንም ዘዴውን ደጋግመው በሥራ ላይ አውለውታል።

ገ/ኢ. ጐርፉ።

*የአባ ጃሌው ታሪክ በእውነተኛ ሰው ሕይወት የተመሰረተ እንጂ ልብ-ወለድ አይደለም። የታሪኩ ኮከብ የሆኑትም ሰው ከመቶ ዓመት በላይ ኖረው ከጥቂት ዓመታት በፊት ከዚህ ዓለም በሰላም አልፈዋል።

***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above poem/article are solely of the author and are not necessarily shared by*** *Meskot*. ***You may contact G.E. Gorfu for comments at*** gegorfu@yahoo.com.